# የኛዋ ብርቱካንስ?

መደበኛ የሥራ ሰዓቴን ጨርሼ እንደተለመደው ወደቤቴ አመራሁ። የቤቴን በር ከፍቼ ስገባ ልጆቼ ተሯሩጠው የተለመደ አቀባበላቸውን ካረጉልኝ በኋላ እኔም ሳም ሳም አድርጌያቸው ሁሌም አረፍ የምልበት ሶፋ ላይ ዝርግፍ ብዬ ቁጭ አልኩ። ዘወትር የምገባበት ሰዓት የምሽቱ ዜና የሚሰማበት ጊዜ በመሆኑ የቴሌቪዥኑን ጣቢያ መቀያየሪያ አንስቼ የእለቱ ዜና የሚገኝበት ላይ ለመቀየር መነካካት ጀመርኩ። ወዲያውም የምፈልገውን ጣቢያ አግኝቼ ማዳመጥ ስጀምር 'የእለቱ ሰበር ዜና' የነበረው ሁለት የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ጋዜጠኞች ዩና ሊ እና ሎራ ሊንግ በሰሜን ኮሪያ አምባገነን መንግሥት ታግተው ከመጋቢት ወር ጀምሮ በ12 ዓመት የከባድ ጉልበት እሥራት ተፈርዶባቸው የነበሩ ናቸው። ምክንያቱም በቻይና በኩል በሕገወጥ መንገድ ገብተዋል እንዲሁም የጠላት ተግባር ፈጽመዋል የሚል ነበር። ያስፈቷቸውም የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት ቢል ክሊንተን ነበሩ።

ደስ የሚል ስሜት ተሰማኝ ምክንያቱም የሰሜን ኮሪያ መንግሥት አምባገነንና የሰብአዊ መብትን የማያከብር በመሆኑ እነዚህም ሁለት ጋዜጠኞች ያለአግባብ መታሰራቸውን ስለተገነዘብኩ ነበር። ግን የተሰማኝ ደስታ ብዙም አልቆየም፡ በሃሳቤ ምናብ ቀጥታ ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ተጓዝኩ፡ የኛዋስ ብርቱካንስ አልኩ፡ እስዋንስ ማን ነው የሚያስፈታት? ማነው የሚነጋገርላት? ብዙ አሰብኩ ብዙ አወረድኩ፡ የቀረበልኝንም እራት ለመብላት ሆዴ እምቢ አለኝ፡ በምግብ ፍላጎት ሳይሆን ሆዴ በሐዘን ይንቦጫቦጭ ጀመር፡ ፈዝዤ ከቀረሁበት ስነቃም ተነስቼ ወደ ኮምፑዩተሬ በመሄድ ዘወትር እየገባሁ የምከታተለውን የፓልቶክ ክፍል ገባሁና ለማዳመት ሞከርኩ፡ ግን የታዘብኩት ማንም ስለብርቱካን የሚወራ ነገር አልሰማሁም ግራ ገባኝ ብርቱካንን ረሳናት እንዴ አልኩ ለራሴ፡ በእለቱ የሚወራው በፈረንሳይ ስለተካሄደው የኢትዮጵያን አመታዊ የስፖርት ፕሮግራም ነበር፡ ሳዳምጥ የነበረው የነበሩትን ችግሮች፣ ምን አህል ተደስተው እንደተመለሱ የመሳሰሉት ነበሩ፡

ሃሳቤ ግን አሁንም ቃሊቲ ነበር፡ ልሰማው የፈለኩት ለምን ብርቱካን አትፈታም፣ ለምንስ አናስፈታትም፣ ለማስፈታትስ ምን ማድረግ አለብን፣ የአለም ሕብረተሰብና መገናኛው ብዙሃን ስለብርቱካን አግባብ በሌለው ሁኔታ መታሰር በይበልጥ እነዲያውቁና እንዲናገሩ ለማድረግ ምን እናድርግ የሚሉትን ሃሳቦች ለመስማት ነበር ጉጉቴ ግን አልሆነም። ተሰላቸሁ፣ ብዙ እናወራለን እንጂ መሥራት ከሚገባን 1/3ኛውን እንኳን የምንሰራ አልመሰለኝም። ግፌት እንፈልጋለን በራሳችን አነሳሽነት ለሐገርና ለሕዝብ ለመስራት የሚገፋፉን ነገር የለም፣ ለምሳሌ ያህል በመጋቢት ወር ውስጥ እነዚሁ ሁለቱ የአሜሪካን ጋዜጠኞች እስር ቤት በተወረወሩበት ወር በካናዳ የሚኖሩ ብርቱካንንና ሐገር ወዳድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ለካናዳ መንግስት የሚቀርብ ብርቱካን እንድትፈታ የሚጠይቅ 10ሺህ የድጋፍ ፊርማ 'Care 2 Action' በሚባለው ድሕረ ገፅ አማካኝነት ለማሰባሰብ ቆርጠው ተነስተው ነበር፡፡ በዚሁ ወቅትም ለእነዚሁ ሁለቱ የአሜሪካን ጋዜጠኞች ይኸው ድሕረ ገፅ ላይ ፊርማ የማሰባሰብ ሥራ ተጀምሮ ነበር፡ ዛሬ ተመልሼ የፊርማው ማሰባሰቡ ሥራ ምን እንደደረሰ ለማየት ወደ ድሕረ ገፁ ገባሁ፡ ባየሁትም አዘንኩ፡ የሁለቱ ጋዜጠኞች 88ሺህ በላይ ሲሆን (http://www.thepetitionsite.com/takeaction/131375038#whosignedthis) የኛዋ ብርቱካን እንኳን 10ሺህ ፊርማ ሊሰባሰብ 2ሺህ የሚሞላም አልተገኘም

(http://www.thepetitionsite.com/11/human-rights-abuse-and-miscarriage-of-justice-in-ethiopia )፡ በጣም አሳዘነችኝ በሚሊዮን ከምንቆጠር የዳያስፖራው ኢትዮጵያዊ ተባብረን ተነጋግረን ካንዱ ወደ አንዱ ተቀባብለን 10ሺህ መሙላት አቃተን? እኔ በበኩሌ አደረኩ ለማለት ሳይሆን ፊርማውን ከመፈረሜም ሌላ ለማውቃቸው ሁሉ በኢ-ሜይል አስተላልፌያለሁ፡ ከጊዜያችን ከሁለት ደቂቃ በላይ ለማትወስድ ይህችን ትንሽ ሥራ መሥራት ካልቻልን ለሐገርና ለወገናችን በተለይ እንደ ብርቱካን ላሉ በእስር ለሚገኙ፡ ከዚህ በፊትም አሁንም ራሳቸውንና ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡና ለመስጠት የተነሱ ወገኖቻችንን በምንድነው የምናበረታታቸው? ወይስ ተስፋ እያስቆረጥናቸው ነው? በጣም አዘንኩ እንባዬ መጣ ለማልቀስ በጣም ፈለግሁ...........አለቀስኩም ግን ማልቀስ መፍትሔ አይመስለኝም።

ወደ መኝታዬ አቀናሁ፣ አልጋዬ ላይ ጋደም አልኩ ነገር ግን እንቅልፍ አልነበረኝም፡ እገላበጣለሁ፡ የብርቱካን መታሰር አልገባኝ ብሏል። ሰው በገዛ ሐገሩ እንዴት ነፃነቱን ያጣል? አሁንም ወደ ቃሊቲ ተጓዝኩ። ብርቱካን ምን እያረገች ይሆን ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡ ከታህሳስ ወር ጀምሮ በቃሊቲ በመከረሚያ ጀግንነቷ ከዷት ይሆን? ተሸንፋ ይሆን ተስፋዋስ ተሟጦ ይሆን? አይመስለኝም ብርቱካን አሁንም ብርቱ ናት አሁንም ጀግና ናት፡ በወገኖቿስ ተስፋ ጥላ ይሆን አልኩ ደግሞ፣ እራሴን ጠየኩት፡ አሁንም አይመስለኝም ነበር የራሴው መልስ፡ የምትተማመነው በሥራዋ ነው፡ የምታመነው እውነትን ነው። እምነት በኛ ቢኖራት ኖሮ አናሳፍራትም ነበር፡ እርሷ ስለሰው ልጆች መብት ማጣት ተቀርቁራ በእምነቷ ፀንታ ስለተገኘት ወደ ዳግም እስር በመወርወሯ እኛ አንድ መሆን ሲገባን የተያያዝነው  እርስ በርስ መከፋፈል ሆኗል፡ ስለሰራችው ገድል አናወራላትም፡ ግን የራሷ ገድል ይናገራል ከቃሊቲ ወጥቶ ይጮሃል እውነት ብትዘገይም ትወጣለች፡ ብርቱካንም በኛም ባይሆን በንፁሕ ሥራዋ ከእስሯ ብቻ ሳይሆን ከዘላለም ባርነትዋ ራሷ ነፃ ወጥታ እኛንም ታወጣናለች።

እናም ሁላችን እንቅልፍ ከሚነሳን ነገር ቶሎ የምንላቀቅበትን የምንፈልግ ከሆነ ክንዳችንን፣ ጉልበታችንን፣ ማንም በፖለቲካ አቋሙ እና አስተሳሰቡ የማይገደልባት ወይም የማይታሰርባት ለሁሉም እኩል የሆነች ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት በሚደረገው ትግል አመለካከታችን ሳይከፋፈል የምንታገልበትና ድምፃችንን የምናሰማበት የማይደክም የማይዝል የትግል መድረክ ያስፈልገናል። አሁን የምናየው ግን ሲሞቅ አለን አለን ሲቀዘቅዝ ደግሞ ደብዛችን የሚጠፋበት አይነት ሁኔታ ይኸው እንደምናየው ብርቱካንን ለማስፈታት እንኳን ጠንካራ የሆነ ትግል ለመድረግ አለመቻላችንን ያመላክታል። ዛሬ ብርቱካን እየተረሳች ነው፡ ድምፃችንን ማሰማት አቁመናል ይህ ደግሞ በጣም ቆሽት የሚያሳርር ነው። በተለይ ባሁኑ ወቅት ከሐገር ፍቅር ይልቅ ለጫትና ለሀሺሽ የበለጠ ፍቅር ያለው ትውልድ (በየቤቱም፣ በሐገርቤትም በውጭም ታይቷል እንዲሁም የፓሪሱ ዝግጅት ግምገማ ብዙ ተብሎበታል) ብርቱካንን ለማስፈታት ይታገላል ብሎ ማስብ በጣም አጠራጣሪ የሆነበት ጊዜ ነው። ግን ምንም ቢሆን ምን አንድ ቁርጠኛ ተከታይ ብርቱካን እንደሚኖራት አልጠራጠርም፤ እሷም አንድዬ ልጇ ሃሌ ናት። ሃሌ ታዳጊዋ፣ ሃሌ ፍልቅልቋ፡ ብርቱካንም ብርቱ እነደሆነች በእኛም ባይሆን ስለ እውነት መኖር ስለ ነፃነት የግድ መኖር ሲባል ትወጣለች። ስሚም የዘለዓለም ነው። ብርቱካንና መላው የፖለቲካ እስረኞች በአስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ።

ፍቅርና ሠላም ያድለን፣ ፍቅሩ ይበልጣል ነኝ።